በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር **185932**

ሐምሌ **30** ቀን **2013** ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑሪዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ መለሰ ዘርጋው አልተጠራም።

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ የቀረበ የለም።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በሂሣቡ ውስጥ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ አለመኖሩን እያወቀ ቼክ ማውጣት ወንጀሎችን ፈፅሟል በሚል የቀረቡበትን ክሶች በመዝገብ ቁጥር 200631 ና 200588 በማጣመር ከመረመረ በኋላ ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት መወሰኑና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ውሣኔውን ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት በመጠየቁ ነው።

በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመዝገብ ቁጥር 200631 የቀረበው ክስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693(1) የተደነገገዉን ክልከላ ተላልፎ ቼኩ በሚወጣበት ወይም ለክፍያ ባንክ በሚቀርብበት ጊዜ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ የሌለው መሆኑን እያወቀ ከሚች አቶ ታደሰ ብሩ ጋር የነበራቸውን የንግድ ግንኙነት መሰረት በማድረግ ሚያዚያ 5 ቀን 2007 ዓ/ም መለያ ቁጥሩ BT 20533394 የሆነውን የንብ ባንክ ቼክ 1,000,000.00 ብር ፅፎና ፈርሞ ሰጥቶት ባንኩ ቼኩን እንዲመዘረው ሚያዚያ 21 ቀን 2007 ዓ/ም ሲቀርብለት የአመልካች ሂሣብ በቂ ገንዘብ የለውም ሲል በመመለሱ፤ በመዝገብ ቁጥር 200588 ደግሞ የወንጀል ሕግአንቀጽ 693(1) የተደነገገዉን ክልከላ ተላልፎ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ የሌለው መሆኑን እያወቀ ታሕሣስ 20 ቀን 2007 ዓ.ም መለያ ቁጥሩ 53390 በሆነው የንብ ባንክ ቼክ 450 ሽህ ብር ፅፎና ፈርሞ ለአቶ ሰሎሞን አማረ ሰጥቶት ጥር 27 ቀን 2007 ዓ/ም ቼኩን እንዲመነዝር የተጠየቀው ባንክ የአመልካች ሂሣብ ገንዘብ የለውም ሲል የመለሰ መሆኑን በመዘርዘር የሚያዝበት ገንዘብ ሣይኖር ቼክ ማውጣት ሁለት ወንጀሎችን ፈጽሟል በሚል ክስ አቅርቦበታል።

አመልካች ድርጊቱን አለመፈፀሙንና ጥፋተኛ አለመሆኑ በመግለፅ ስለተከራከረ የስር ፍርድ ቤቱ የግራቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ በአምስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል። ይህን የጥፋተኝነትና የቅጣት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ውሣኔ በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች ላይ የተወሰነውን የጥፋተኝነት ሆነ የቅጣት ውሣኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተብሎ እንዲታረምለት የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል።

አመልካቹ ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው አንድ ሰዉ ወንጀል ፈፅሟል የሚባለዉ

በወንጀል ሕግ አንቀፅ 23(2) ስር የተዘረዘሩት የሕጋዊ፣ የግዙፋዊና የሞራላዊ መመዘናዎች ሲሟሉ ብቻ ሆኖ ሣለ አመልካች ቼኮችን የሰጠው ተቀባዮች እንዲመነዘሩት ሣይን በነበራቸው የንግድ ግንኙነት ለዋስትና መሆኑ በተረጋገጠበት ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ መቀጣቱ፤ ወንጀሉን ፈፅሟል ቢባል እንኳ ተበዳዮችን ለመጉዳት ሣይሆን ለዋስትና ተብሎ የተሰጠ ቼክ መሆኑ ግምት ውስጥ ገብቶ በቸልተኝነት በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ማውጣት ወንጀል ጥፋተኛ መባል ሲገባው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 693(1) ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቼክ ከአመልካች የተሰጠበት ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል ከነበረዉ የንግድ ግንኙነት በመሆኑ አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 693(1) ወይስ በ693(2) ነዉ? በሚለዉ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ተመርምሮ እንዲወሰን ታዞ የፅሁፍ ክርክሩ ቀርቧል።

ተጠሪ በበኩሉ በቂ ገንዘብ ሣይኖር ቼክ በሰጠ ሰውና በቼክ ተቀባዮች መካከል የንግድ ግንኙነት መኖሩ ቢረጋገጥ እንኳ በቂ ገንዘብ የሌለውን ቼክ በማዉጣት የተፈፀመውን የወንጀል ድርጊት ሕገወጥነቱን  የማያስቀረው መሆኑን፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 693(1) ስርየጠደነገውን ወንጀል ለማቋቋም በተከሣሹ የወጣው ቼክ ወደ ባንክ ለክፍያ ሲቀርብ በቼክ አዉጭዉ ሂሳብ ዉስጥ በቂ ገንዘብ አለመኖሩን መረጋገጡ ብቻውን በቂ መሆኑን፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት  በመዝገብ ቁጥር 149071 በተሰጠዉ ትርጉምም አንድ ቼክ በሚወጣበት ጊዜ ወይም ለክፍያ በቀረበበት ጊዜ  በቼክ አዉጭዉ ሂሳብ ውስጥ ለክፍያ የሚሆን በቂ ስንቅ(ገንዘብ) አለመኖሩ እየታወቀ ቼክ የተሰጠ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ከግል ተበዳዮች ጋር ያለዉ ግንኙነት መሰረት ተደርጎ የተከሳሽ የወንጀል ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀመ ነው ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ  የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ተከራክሯል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚጠናክር የመልስ መልስ ክርክር አቅርቧል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በማስቀረቢያ ነጥቡ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል። እንደመረመርነው በዚህ ችሎት መልስ እንዲሰጠው የተፈለገው ነጥብ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን እያወቀ ቼክ አውጥቷል የሚል የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰው በቼክ አውጪውና በተቀባዮ መካከል የንግድ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ብቻ ተከሣሹ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 693(2) ድንጋጌ ስር መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ነው።

በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች ቼኮችን ለተቀባዮች አለመስጠቱን ወይም ቼኮቹ ሲወጡም ሆነ ለክፍያ ሲቀርቡ በሂሣቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ የነበረው ስለመሆኑ አልያም በቂ ገንዘብ የሌለው መሆኑን ማወቅ የማያስችለው ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ያጋጠመው ስለመሆኑ አልተከራከረም። የአመልካች ክርክር ቼኮችን ለተቀባዮች ፅፎና ፈርሞ የሰጠው በመካከላቸው የነበረውን የንግድ ግንኙነት መሰረት በማድረግ ለዋስትና እንዲሆናቸው እንጅ እንዲመነዝሩት አይደለም የሚል ነው። ከላይ እንደተገለፀው ለዋስትና መሰጠቱ ቢረጋገጥ በተከሣሹ የወንጀል ሐላፊነት ላይ የሚያስከትለው ለውጥ መኖር አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 166392 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት በመዝገብ ቁጥር 161448 በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የቀረበ ማረጋገጫ የለም።

በመሆኑም አመልካች እንደሚቀርበው ክርክር ቼኮችን ለዋስትና ስለመስጠቱ የሚያረጋግጡ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች አቅርቦ ሣያረጋግጥ ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኝነት ድርጊት ነው ተብሎ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 693(2) ስር ጥፋተኝነት ውሣኔ አለመሰጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በሚል የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለና የሚያሣምን ክርክር ሆኖ አላገኘነውም።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ  ድ  ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም  ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ  አፈጻጸም  ዓላማ  አያገለግልም

በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የወሰነውን ቅጣት በሚመለከት የተፈፀመ ስህተት ባይኖርም በአሁኑ ሰዓት በዓለምና በሐገራችን የተፈጠረውን የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተወሰበት ቅጣት መሰረት ማረሚያ ቤት በመግባቱ ለልጆቹ እና ባለቤቱ የቤት ኪራይ የሚከፍሉት ገንዘብ በማጣት በተለያዬ ዘመድ ቤት እየተጠጉ በመኖር ላይ መሆናቸውን ታሣቢ በማድረግ ከአጠቃላይ የቅጣት ዓላማና ግብ አንፃር እንደገና መወሰን ያለበት መሆኑ ታምኖበታል፡፡

በዚህም መሰረት የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችን በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በእያንዳንዱ የወንጀል ክስ መነሻ ቅጣት በመያዝ የሁለቱን አጠቃሎ በመደመር ሰባት ዓመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራትን በመነሻነት ይዞ በአንድ ማክበጃ ምክንያት በአንድ እርከን ከፍ እንዲል ካደረገ በኋላ ሶስት ማቅለያ ምክንያቶች ከእርከን 25 ወደ እርከን 22 ዝቅ እንዲል ማድረጉ ተገቢ ሆኖ በተጨማሪ አመልካች በሰበር ሰሚ ችሎቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 188(5) ድንጋጌ መሰረት አመልካች በዋስትና ግዴታ ሆኖ የሰበር ክርክሩን እንዲከታተል በሰጠው መሰረት ከማረሚያ ቤት ከወጣ በኋላ በየቀጠሮው መቅረቡንና በቤተሰቦቹ በኩል በተደጋጋሚ መፀፀቱን፤ ከሰዎች ለምኖ ያኘውን ገንዘብ ለግል ተበዳይ መክፍሉን ባቀረበው አቤቱታ በማረጋገጡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የገንዘብ እጦት በማረጋገጥ ከገነዘብ ቅጣት ነፃ ማድረጉን ታሣቢ በማድረግ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82(1)(ሠ) መሰረት፤ እንዲሁም በደረሰበት ኪሣራ ለቤት ኪራይ የሚከፈል ገንዘብ በመጥፋቱ ባለቤቱና ልጆቹ በመዘድ ቤት በየተራ መኖር መጀመራቸውን ሕፃናት ልጆቹ ከፍተኛ ችግር ውስጥ መግባታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት ሁለት ማቅለያ ተይዞለት ከእርከን 22 ወደ እርከን 20 ዝቅ አንዲል ተደርጎ በዚህ ጉዳይ የታሰረው ሁሉ ታሣቢ ተደርጎለት በአራት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

በአመልካች የተወሰነውን የእስራት ቅጣት አፈፃፀም በሚመለከት መፈፀም ከሚገባው የአራት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት ቅጣት ውስጥ ከጥር 27 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ እስከ የካቲት 18 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ በድምሩ ሁለት ዓመት ከሃያ ቀን አካባቢ በማረሚያ ቤት በመቆየቱ ከተወሰነበት ቅጣት ግማሽ አካባቢ መፈፀሙን እንዲሁም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 201 እና 202 ድንጋጌ መሰረት በአመክሮ ቢፈታ የሚቀረውን የእስራት ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት በተለይም በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን በከፍተኛ የኮረና ወረርሽን ውስጥ የምትገኝ በመሆኑ አመልካች ተመልሶ ወደ ማረሚያ የሚገባ ከሆነ ሕፃናት ልጆቹ ለመኖር ከፍተኛ ችግር የሚገጥማቸው መሆኑን ታሣቢ በማድረግ ቀሪ የታሰረው በቂ ነው በሚል ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሣኔ</u>

1) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 200631 እና 200588 የቀረበውን የወንጀል ክርክር መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 200631 ላይ በማጣመር ጥር 27 ቀን 2011 ዓ/ም እንዲሁም የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 176237 መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ/ም ከጥፋተኝነት አንፃር የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 200631 የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የወሰነው ቅጣት እንዲሁም የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 176237 መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ/ም ከቅጣት አኳያ የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 2(ለ)(2) መሰረት የእስራት ቅጣቱ በአራት ዓመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እንዲሆን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተሻሽሎ ተወስኗል። አመፈፃፀሙን በሚመለከት ከላይ በፍርዱ ላይ በተገለፁት ምክንያቶች አመልካች እስካሁን የታሰረው በቂ ነው ተብሏል።

## ትዕዛዝ

1) አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት የገባው የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል ያስያዘው ገንዘብ ይመለስለት።
2) በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት የተሻሻለና የታሰረው በቂ እንዲሆን የተወሰነ መሆኑን እንዲያውቅ የውሳኔው ቅጅ ለአ/አ ማረሚያ ቤት ይላክለት።
3) መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም